በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# … ተጠበቁ!!!

**መምህር፡-  ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**


**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

***<u>ቦታ፡-</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን  አዳራሽ

በየሳምንቱ  ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ነሐሴ  ፳፫  ቀን  ፳፻፬  ዓ.ም.


A NEW YORK TIMES BESTSELLER
NEALE DONALD WALSCH
CONVERSATIONS WITH GOD
AN UNCOMMON DIALOGUE
READ BY THE AUTHOR
WITH EDWARD ASNER & ELLEN BURSTYN


NEALE DONALD WALSCH
'Contains a wisdom I believe we all have inside us but don't stop to listen to . . .
There is the wisdom of the ages in this book.'
DR BERNIE SIEGEL
Conversations with God
- The Movie
An uncommon dialogue
THE INTERNATIONAL BESTSELLER



... ተጠበቁ

## *የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አደጋዎች*

## *መግቢያ*

- በዘመናችን ክርስቲያናዊ መልእክት የሚያስተላልፉ መስለው ብዙዎችን እያሳቱ ወደ ጥፋት የሚያደርሱ መጻሕፍት፣ ቪዲዮ ፊልሞች ወዘተ በመሠራጨት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም መካከል Conversations with God (1,2,3) and Conversations with God for Teens የሚሉ መጻሕፍትና ፊልም የሚጠቀሱና ብዙዎችን እየጎዱ የሚገኙ ናቸው፡፡
- መጻሕፍቶቹ በ Neale Donald Walsch የተጻፉ ሲሆኑ ርዕሶቹን ብቻ በቀላሉ ስንመለከት ጎጂ መስለው አይታዩም እንጂ እስካሁን ከደረሰው ጉዳት የላቀ አደጋ በብዙዎች ጽኑ ሃይማኖት (እምነት)- በክርስትናችን ላይ እያሳደሩ ነው፡፡
- እነዚህ መጻሕፍት በ New York Times Best Sellers ዝርዝር ውስጥ ለወራት ቆይተዋል፡፡

# <u>ተጠበቁ</u>

## *የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አደጋዎች*

### *መግቢያ*

- እነዚህና ሌሎችም መጻህፍት በ Oprah Winfrey’s Book Club ዝርዝር ውስጥ መካተታቸው የሚደርሰውን መንፈሳዊ አደጋ ከፍ ያደርገዋል፡፡

### የመጽሐፉ ይዘት

- ጸሐፊው ከልጆች የሚቀርቡለትን የተለያዩ ጥያቄዎች ‹‹የእግዚአብሔርን ድምጽ›› በመጠቀም እመልሳላሁ በማለት ይህንኑ ማድረጉን ይጠቁማል፡፡

### *የመጽሐፉ አደገኛነት*

- ይህን መጽሐፍ አደገኛ የሚያደርገው ‹‹የክርስቲያኖች መጽሐፍ›› ተብሎ በገበያው ላይ በስፋት መሠራጨቱ ነው፡፡

# ተጠበቁ

## *ከመጽሐፉ የተቀነጨቡ*

- ‹‹ስሜቶችህን አዳምጥ… ስሜቶችህን ተከተል… ስሜቶችንህ አክብራቸው… ስሜቶችህ ወደ ‹‹ችግር›› እንደማይከቱህ ተማመን፡፡ ምክንያቱም ስሜቶችህ የአንተ እውነት ናቸውና፡፡›› Conversations with God Vol 1 ገጽ 14-15
- “በራስህ ልታደርገው የምትችለውን ማንኛውንም ነገር አድርግ፣ ማናቸውንም ባሕላዊ ልማዶች፣ በዓላቶችን፣ ተመስጦዎችን፣ ሐሳቦችን፣ ዘፈኖችን፣ ቃላቶችን፣ ድርጊቶችን ሁሉ ያለመቆጠብ አከናውናቸው ተሳትፎ አድርግባቸው፡፡ ይህንም እኔን በማመን ፈጽም - ይልሃል እግዚአብሔር›› ይላል፡፡ Conversations with God Vol 2 ገጽ 22

# ተጠበቁ

## *ተጠቃሽ ምሳሌዎች*

- አንዲት ሴት ‹‹ሌዝቢያን (ግብረ ሰዶማዊት) የሆንኩት ስለምንድር ነው?›› ብላ ላቀረበችለት ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥቷል፡፡
- ‹‹ሌዝቢያን (ግብረ ሰዶማዊት) የሆንሽው ሌዝቢያን (ግብረ ሰዶማዊት) ሆነሽ ስለተወለድሽ ነው፡፡ ይህም ማለት ባለ ሰማያዊ ቀለም ዓይን፣ ባለ ቀኝ እጅ ሆነሽ እንደተወለድሽው ማለት ነው፡፡››
- ምክሩን በመቀጠልም በሁሉም ሰው ፊት ‹‹ሌዝቢያንነትዋን (ግብረ ሰዶማዊትዋን) ብሎም ልዩነትዋን›› ‹‹እንድትኮራበት - ደስታዋንም እንድትገልጽበት›› ይመክራታል፡፡

# <u>ተጠበቁ</u>

## *ተጠቃሽ ምሳሌዎች*

- ሌላዋ ሴት ደግሞ ‹‹አሁን የምኖረው ከወንድ እጮኛዬ ጋር ነው፤ ወላጆቼ ግን እንዲህ ያለ ኑሮ ኃጢአት ስለሆነ በሕግ በሥርዓት ተጋቡ ብለው ይመክሩኛል፡፡ ስለዚህ በግድ እርሱን ማግባት ይገባኛልን?›› ብላ ላቀረበችለት ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥቷል፡፡
- ‹‹የምትበድይው በፊቱስ ኃጢአት የምትሠሪው ማነው? እኔ እግዚአብሔር በፊቴ ምንም ኃጢአት እንዳልሠራሽ አውቃለሁና አትጨነቂ፡፡››
- ሌላው የተጠየቀው ጥያቄ እግዚአብሔር ስሚያደርግልን የኃጢአት ሥርየት ሲሆን በእግዚአብሔር ቦታ ሆኖ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ‹‹ይቅር እል ዘንድ የተሠራ ኃጢአት የለምና ማንንም ይቅር ስል አታገኙኝም፡፡ አሁን እንደምትነግሩኝ ሰዎች ትክክል ያልሆነውን እርስ በርስ መፈራረድን መርጠዋል፤ እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ የሚለውን ሕጌን ራስተዋል፡፡ ኃጢአት ስለሌለ ሥርየትም አያስፈልግም…›› ይላል፡፡

# ተጠበቁ

## *የደራሲው ወይም የጸሐፊው መልእክት*

- የጸሐፊው የዋልሽ ፍልስፍናዎች በሚከተሉት አራት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ተካተው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡
  1. ሁላችንም አንድ ነን፡፡
  2. ሰዎች የሚያስፈልገንን ሁሉ አለን፡፡
  3. ሰዎች ምንም ነገር ማድረግ ወይም መድከም አይጠበቅብንም፡፡
  4. ሰዎች መንገዳችን ሌላኛው አማራጭ መንገድ እንጂ የተሻለው አይደለም፡፡

<u>ተጠበቁ</u>

## *ማጠቃለያ*

- ጸሐፊው ዋልሽ የሚያስተጋባው ‹‹ሁሉ አንድ ነው አንዱም ሁሉን ነው›› የሚለውን የሞኒዝም እና ‹‹ሁሉም እግዚአብሔር ነው እግዚአብሔርም ሁሉን ነው፡፡›› የሚለውን የፓንቴይዝምን አስተሳሰብ ነው፡፡
- ይህ ጸሐፊ (ደራሲ) መጽሐፍ ቅዱስን (ጥቅሶች) በተደጋጋሚ የሚጠቅስ ሲሆን ይህም መጽሐፍ ቅዱስን ለገዛ ሐሳባቸው የሚጠቀሙበት ሰዎች መታወቂያ ምልክት ነው፡፡
- በአጠቃላይ የደራሲው ዋና መልእክት ምንም መለወጥም ሆነ መስተካከል ሳያስፈልገን እኛ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ነን የሚል ነው፡፡
- ይህና ይህን የሚመስሉ መጻሕፍት በት/ቤቶች ለሚገኙ ሕፃናት፣ ታዳጊዎችና ወጣቶች በመሸጥ ላይ ይገኛሉ፡፡
- ስለዚህ ለልጆቻችን ምግብ ሆኖ የቀረበው ይህ መርዛማ ነገር ምን እንደሆነ አውቀን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡

# <u>ተጠበቁ</u>

## *ተጠንቀቁ*

- ‹‹እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ።›› ***<u>ቆላ 2፡8።</u>***
- ‹‹ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም።ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ።እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ።አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።›› ***<u>ካል ጢሞ 4፡2-5።</u>***
- ‹‹እንግዲህ እናንተ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ፥ በዓመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ፤ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ። ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።›› ***<u>ካል ጴጥ 3፡17-18</u>***

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org